# ወደዚያ ሂጂልኝ !

እንዴት ያደርግሻል የያዘሽ አባዜ
ስንቱን ቀላመድሽው በዚች አጭር ጊዜ
ከምን የዋለች ጊደር ምን ተምራ መጣች
በቶሎ ተማርሽው እውነትም ፈጠነች፡፡

እድሜም አላነሰሽ እውቀትሽም በቂ ነው
እንደ ክፉ በቅሎ መራገጥሽ ምነው
ፍትሕ ትሰጭያለሽ ተብለሽ ተነግሮ
ባንቺው ብሶ ታዬ ለዚያውም ዘንድሮ

አንቺንስ ሲያሰልፍሽ ከጀግኖቹ ጋራ
ለካስ አስልቶ ነው እንድትሆኝ ደንቃራ
ገና ከጅምሩ ጽሑፍ ሲያወጡልሽ
በጣም አፍረን ነበር ያኔ ዝም ማለትሽ

ሕይወት እኮ ከፍሏል አይደለም በከንቱ
ጀግና ያገኘ መስሎት ሕዝብሽ መሰዋቱ
አሜሪካ ትስሄጅ እንዲያ መዘንጋቱ
በሊሞ መንሸርሸር ጭፈራ ማብዛቱ
እንዲያው አንቺን አያርገኝ አይቀር መገባቱ፡፡

ሕዝቡ አልመረጠሽ ብርሃኑ እንጂ
በሞቱት አጥንት ላይ ስትረማመጂ
የዘር ሀረግ ማንሳት የያዘሽ በሽታ
አይቀር ቅልቅሉ የማታ የማታ
መንገድሽ ግልጽ ነው ከወያኔ ተርታ፡፡

እስቲ ልጠይቅሽ እንደው አንድ አፍታ
በስብሰባ አዳራሽ ተቀምጠ በርጋታ
ትግሬ ይሁን አፋር ወይም ወላይታ
ኦሮሞም ጉራጌ አማራ ከምባታ
በምን አወቅሽ ዘሩን የጠፋው ከተርታ
ይቅርታ ያሰኘሽ የያዘሽ በሽታ
እጅግ ያሳፍራል ከዘር ጋር ጨዋታ
ወያኔን ሆንሽብኝ የልቡ ትርታ፡፡

በቃኝ ብዬሻለሁ ፍቅርሽ ወጥቶልኛል
ዘረኛ ስለሆንሽ እጅጉን መሮኛል
ወደዚያ ሂጂልኝ ስራሽ ከርፍቶኛል
ፍርዱን ያገሬ ሰው ስትሄጅ ይከፍልሻል፡፡